# ገለል



የጽናት፣ የእምነት ምልክት
        የኢትዮጵያዊነት ሞገስ፣ ግርማ
የሰማእትነት ክብር
        የመስዋእትነት፣ የድል ዓርማ
የአቡነ ጴጥሮስ ማስታወሻ
የመሪነት አሻራ፣ የጀግንነት ቅርስ ማውረሻ
የሕዝብ አባትነትን
ሃይማኖታዊ ብቃትን
የአቋም ጽኑነትን
የትውልድ ምሳሌነትን
ያሳየ . . .
የነጻነትን ትርጉም
        በሕያው ገድል የተከለ
ሐውልቱም እንቅፋት ሆኖ
        «መንገድ ልቀቅ!» ተባለ?!
ያገር ባለውለታ
        ያገር ኩራት እንዳልነበር
ሁለተኛ ሞት ይሙት?
        ዳግመኛ ቀብር ይቀበር?!
ለነገሩ . . .
ክፉ ነውና ዘመኑ
        ቃል የተካደበት፣ እምነት የፈረሰበት
ማንነት የቆሸሸበት፣ ውርደት የሰፈነበት
ለእውነት መቆም፣ መመስከር
        እንደ ሰማይ የራቀበት
ታሪክ፣ ቋንቋ ተዋርዶ
አንድነት፣ ድንበር ተንዶ
አይቷልና ሐውልቱ . . .
መርጦ ይሆን ዞር ማለቱን
ፊቱን ሸፍኖ መለየቱን?
ይህንን የዘመን ውጥንቅጥ
        ሰልችቶት ይሆን መመልከቱ?
ለዘመናት ከኖረበት ተከናንቦ ዞር ማለቱ?
ሐውልቱ . . .



---

ቴዎድሮስ አበበ
ግንቦት ፯ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም. | May 15, 2013
Washington, D.C.